15ኛ ዓመት ቁጥር 12
15th Year No. 12

ባህር ዳር መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ/ም
Bahir Dar April 1, 2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

| | | |
|---|---|---|
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State | ✉ 1324<br>ያንዱ ዋጋ ብር 4.40<br>Unit price 4.40 |


| ማውጫ | Content |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 175/2002 ዓ.ም<br>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማና አርማን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ | Proclamation No. 175/2010<br>A PROCLAMATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE FLAG AND EMBLEM OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE |

## አዋጅ ቁጥር 175/2002 ዓ.ም
## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማና አርማ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የራሱ ሰንደቅ ዓላማ እና አርማ እንደሚኖረው በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 3 የተደነገገ በመሆኑ፤

ይህንኑ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በስራ ላይ ያለውን የብሔራዊ ክልሉን ሰንደቅ ዓላማ እና አርማ በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮችን በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 175 /2010
## THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE FLAG AND EMBLEM PROCLAMATION

**WHEREAS**, Article 3 of the Revised Constitution of the Amhara National Regional State stipulates that the Region will have its own Flag and Emblem;

**WHEREAS**, it is found necessary to promulgate a law providing depending on the provision of the Constitution, providing for particulars on the Flag and Emblem of the National Region;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀፅ 3(1) መሠረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማና አርማ አዋጅ ቁጥር 175/ 2002 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ :-

1. "በስተቀኝ" ማለት በፌደራል መንግስቱ አዋጅ ቁጥር 654/2001 ዓ/ም አንቀጽ 2(4) እንደተደነገገው "አንድ ሰው ፊቱን ወደ ተመልካች አቅጣጫ በማድረግ ሰንደቅ ኣላማዎች በሚቆሙበት ወይም በሚሰቀሉበት ወይም ባሉበት መስመር መሐል ሲቆም የሚኖረው የቀኝ እጅ አቅጣጫ" ማለት ነው ፡፡
2. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በብሔራዊ ክልሉ የግዛት ወሰን ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 49 sub article 3(1) of the Revised Constitution of the Amhara National Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Amhara National Regional State Flag and Emblem proclamation No. 175/2010."

### 2. Definitions

In this Proclamation:

1. "On the Right" means as it has been declared under Article 2(4) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Flag proclamation No. 654/2009, "on the extreme right with reference to the direction of a person standing in the line of Flags facing Observers".
2. "Person" means a natural or juridical person.

### 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable within the territorial boundary of the Amhara National Regional State.

## ክፍል ሁለት

## ስለብሔራዊ ክልሉ ሰንደቅ አላማና አርማ

### 4. የሰንደቅ ዓላማ ምንነት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ / ከዚህ በኋላ "ሰንደቅ ዓላማ " እየተባለ የሚጠራው /የክልሉ ሕዝቦች ወሣኝነት መገለጫ ሲሆን፣ ከሌሎች የአገሪቱ ህዝቦች ጋር በአንድነት፣ በፍቅርና በመተሳሰብ አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነትና ተስፋ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

### 5. የሰንደቅ ዓላማ ቀለማትና ቅርፅ

1. ሰንደቅ ዓላማው ከቀኝ እና ከግራ በቢጫ መደብ ላይ የሚያርፉ ሶስት ጐንዮሽ ቅርፅ ያላቸው ቢጫ መደቦች እንዲሁም በመካከሉ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ቀይ መደብ ይኖረዋል፡፡
2. ቀለማቱ ብሩህና መሠረታዊ ይሆናሉ ፡፡
3. በሰንደቅ ዓላማው ቀዩ መደብ መሃል ላይ ባለ አምስት ልሳን ቢጫ ኮከብ ይኖረዋል፡፡
4. ግራና ቀኝ የሚገኙት ቢጫ መደቦች እኩል መጠን ሲኖራቸው የሰንደቅ ዓላማው ቀዩ መደብ የነዚሁ ድምር ስፋት ይኖረዋል፡፡
5. የሰንደቅ ዓላማው ወርድ የቁመቱ እጥፍ ይሆናል፡፡

## PART TWO

## THE FLAG AND EMBLEM OF THE NATIONAL REGION

### 4. Symbolism of the Flag

The Flag of the Amhara National Regional State (hereinafter "the Flag") symbolizes the decisiveness of the peoples of the Region; and reflective of their belief and hope to live together in love and common will with other peoples of the Nation in unity thereof .

### 5. Colors and Shape of the Flag

1. The Flag shall have yellow color set on the triangle shape at the right and left with yellow background, and the rectangle shape at the centre having red background.
2. The colors shall be bright and basic.
3. The five sided yellow star shall be set on the red background at the center of the Flag.
4. The left and right part of the yellow background shall be equal size and their sum equal to the red background of the Flag.
5. The Flag's width shall be twice of the length.

## 6. የሰንደቅ ዓላማው ትርጉም

የሰደንቅ ዓላማው ቀለማትና በሰንደቅ አላማው ላይ የሚያርፈው ኮከብ የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል፡-

1. ቢጫው፣ የአማራ ክልል ህዝቦች የብሩህ ተስፋ ምልክት ሆኖ መጭውን የክልሉን ህዝቦች የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልፅግና ብሩህ ተስፋ ያመለክታል፤
2. ቀዩ፣ የአማራ ክልል ህዝቦች ለሠላም፣ ለዴሞክራሲና ለነፃነት ያደረጉትን የመሰዋእትነት ተጋድሎና ድል ያመለክታል፣
3. ኮከቡ ፣ የአማራ ክልል ህዝቦች ከሌሎች ህዝቦች ጋር በአንድነት፣ በፍቅርና በመተሳሰብ ለመኖር ያላቸውን እምነትና ተስፋ ያንፀባርቃል፡፡

## 7. የሰንደቅ ዓላማ ስዕላዊ መልክ

የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ እንደሚከተለው ነው ፡-

## 6. Meaning of the Flag

The colors of the Flag and its Star shall represent the following meanings:

1. The Yellow being the sign of the bright hope of the peoples of the Amhara Region shall indicate the bright hope of the Region future economic and social prosperity of the peoples of the Region ;
2. The Red shows struggle and sacrifice of the peoples of the Region of Amhara and victory for their peace, democracy and freedom;
3. The Star reflects the belief and hope of the peoples of the Amhara Region to live with other peoples in unity, love and common will.

## 7. Pictorial Representation of the Flag

The Pictorial representation of the Flag is as follow:



## 8. ስለ ክልሉ መንግስት ዓርማ፣ ምንነትና ትርጉም

1. የብሔራዊ ክልሉ ዓርማ /ከዚህ በኋላ "አርማ" እየተባለ የሚጠራው / የክልሉ ህዝቦች ለሰላም፣ፍትህና ዲሞክራሲያዊ እድገት ያላቸውን ጽኑ እምነት የሚወክል፣ለታሪካቸውና ባህላቸው ቀናኢ መሆናቸውንና የኢኮኖሚ መሰረታቸውም የእርሻና ኢንዱስትሪ የተደጋገፈ እድገት መሆኑን የሚያንፀባርቅ ልዩ መታወቂያ ምልክት ነው ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የብሔራዊ ክልሉ ዓርማ ቅርጽ ክብና በመሃሉ የእርግብ አምሳል ያረፈበት ሚዛን፤ ከሚዛኑ ስር የላሊበላና የፋሲል ግንብ እንዲሁም የጢስ አባይ ፏፏቴን የያዘ ሆኖ፤ ዙሪያው በስንዴ ዘለላና በማሽን ጥርስ / ጊር/ የታቀፈ ይሆናል፡፡

3. አርማው አረንጓዴ መደብ ይኖረዋል፡፡

4. አርማው የሚከተለው ስዕላዊ መልክ ይኖረዋል፡-

## 8. The Regional Government Emblem, Symbolism and Meaning

1. The emblem of the National Region (hereinafter referred to as "Emblem") represents the strong belief of the peoples of the Region for peace, justice and democratic development; as well as in special symbol of identity of their integrity for agricultural and industrial development .

2. Without prejudice to sub article 1 of this Article, the shape of the emblem of the National Region shall be at the centre there is a balance with a dove and there under the Castle of Lalibela and Fasil as well as the Tis Abay water fall; embraced there with Wheat and the Machine Gear.

3. The Emblem shall have the green background.

4. The Emblem shall have the following pictorial representation:



5. በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤

ሀ/ የስንዴ ዘለላው፣የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ፣

ለ/ ጊሩ ፣ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ፣

ሐ/ ርግቡ ፣ ሰላምን፣

መ/ ሚዛኑ ፣ ፍትህና ዴሞክራሲን፣

ሠ/ የላሊበላና የፋሲል ግንብ ፣የክልሉን ታሪክና የቅርስ ሃብት ፣

ረ/ የጢስ አባይ ፏፏቴ ፣ የክልሉን የተፈጥሮ ሃብት እና

ሰ/ አረንጓዴው መደብ ፣ሥራን፣ልምላሜን እድገትንና የብሔራዊ ክልሉን ህዳሴ የሚወክሉ ይሆናሉ ፡፡

5. Without prejudice to sub article (1-3) of this Article;

a. The Wheat represents the Agricultural Economy,
b. The Gear represents the Industrial Economy,
c. The Dove represents peace,
d. The Balance represents Justice and Democracy,
e. The Castle of Lalibela and Fasil represents the Region’s history and fossil resources,
f. The Waterfall of Tis Abay represents the natural resources of the Region, and
g. The Green background represents job, fertility, development and the renascence of the National Region.

## ክፍል ሦስት
## ስለ ሰንደቅ አላማው አጠቃቀም

## PART THREE
## USE OF THE FLAG

### 9. የሰንደቅ ዓላማው መጠንና አጠቃቀም

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው የሚከተለው መጠን ይኖረዋል ፡-

1. በከፍተኛ አደባበይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 210 x 420 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት ከ15-18 ሜትር ፣

2. በመካከለኛ አደባበይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 150x300 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት ከ10-15 ሜትር ፣

### 9. Size and Use of the Flag

Without prejudice to Article 6 of this proclamation, the Flag shall have the following sizes:

1. at major squares, the size of the Flag shall be 210 x 420 centimeters and the Flag staff shall be from 15 to18 meters high;

2. at medium squares, the size of the Flag shall be 150 x 300 centimeter and the Flagstaff shall be from 10 to 15 meters high;

3. በመስሪያ ቤቶች ፤በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ድርጅቶች አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 135 x270 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 10-12 ሜትር ፣
4. በትልልቅ የመንግስት ህንፃዎች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 135x270ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 5 ሜትር ፣
5. በትልልቅ ህንፃዎች ምድር ቤት ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችና የንግድ ቤቶች የሰንደቅ ዓላማው መጠን 105x210 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 3 ሜትር ፣
6. በሰልፍ ጊዜ በክብር ዘብ የሚያዘው የሰንደቅ ዓላማ መጠን 105x210 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 230 ሴንቲ ሜትር ፣
7. በብሔራዊ ክልሉ ፕሬዘዳንት እና በክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት ጠረንጴዛ ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 21x42 ሴንቲ ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 30 ሴንቲ ሜትር ሆኖ ይዘጋጃል ፡፡
8. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፤ የብሔራዊ ክልሉ ፕሬዚዳንት በሚጓጓዝበት መኪና ላይ የሚውለበለበው ሰንደቅ ዓላማ የቁመቱና የወርዱ ቅንብር / ሬሾ / 3በ4 ሆኖ 30 በ 40 ሴንቲ ሜትር ይሆናል ፡፡

3. at the squares of offices, higher education institutions and organizations, the size of the Flag shall be 135 x 270 centimeters and the Flag staff from 10 to12 meters high;
4. on major government buildings, the size of the Flag shall be 135 x 270 centimeters and the Flag staff shall be 5 meters high;
5. at Organizations and business enterprises on the ground floors of major buildings, the size of the Flag shall be 105 x 210 centimeters and the Flag staff shall be 3 meters high ;
6. during procession the size of the Flag holding with guard of honor, shall be 105 x 210 centimeters and the Flagstaff shall be 230 centimeters high;
7. on the desks of the offices of the National Regional President and the Speaker of the Regional council, the size of the Flag shall be 21 x 42 centimeters and the Flag staff shall be 30 centimeters high; and
8. Without prejudice to the provisions of this Article, on vehicles in which the National Regional President travels, the width and length of the Flag shall be in the ratio of 3:4 and shall be 30 by 40 centimeters.

## 10. የሰንደቅ ዓላማው አሰቃቀል

1. የሰንደቅ ዓላማውን መውለብለብ የሚያግድ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር ፤ በክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤት፣ በርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ፣ ከላይ እስከታች ባሉ የክልሉ የተዋረድ መንግስታዊ ተቋማት ጽህፈት ቤቶች ፣በፍርድ ቤቶችና በትምህርት ቤቶች ፣ ሰንደቅ ዓላማው በየቀኑ ይውለበለባል ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ያልተመለከቱ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በብሔራዊ በዓላት ቀን ሰንደቅ ዓላማ ይሰቅላሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ አላማ የሚሰቀለው በሚከተሉት ስፍራዎች ይሆናል፡-

   ሀ/ በክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ፤

   ለ/ በርዕሰ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ ፡፡

4. የዚህ አንቀፅ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በክልሉ ውስጥ በሚካሄደው አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ሰንደቅ ዓላማው መራጮች በሚመዘገቡበት እና ድምጻቸውን በሚሰጡበት ቦታ ይሰቀላል፡፡

## 10 . Display of the Flag

1. Except in case of *force majeure* obstructive to having it flown, the Flag shall fly daily at the Secretariat of the Regional Council, at the Secretariat of Regional Government, at Offices of hierarchically lower level governmental organizations, at Courts and Schools.

2. Government Offices not specified in sub article (1) of this Article shall fly the Flag on public holidays.

3. Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article the Flag shall fly at the following places:

   a. At the square with in the premises of the Secretariat of the Regional Council;

   b. At the square with in the premises of the Secretariat of the Regional Government.

4. Without prejudice to the generality of this Article, the Flag shall be flown at the place where registration or casting takes place during the National and Regional election.

## 11. ሰንደቅ አላማው ከሌሎች አርማዎች ጋር ስለሚኖረው አያያዝ

1. ከሌላ ወይም ከሌሎች አርማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲወጣ ሰንደቅ አላማው በስተቀኝ ይውላል ፡፡
2. ከሁለት አርማዎች ጋር ብቻ ሲያዝ ወይም ሲወጣ ሰንደቅ አላማው ከመሃልና በቁመቱ ልክ ከፍ ብሎ እንዲውል ይደረጋል ፡፡

## 12. ስለ ሰንደቅ ልሳን

የማንኛውም ሰንደቅ ልሳን (ጫፍ) ግማሽ የክብ አምሳል ይኖረዋል፡፡

## 13. ስለ ሰንደቅ መትከያ ስፍራ

በአደባባይ የሚውለበለብ ሰንደቅ ዓላማ ሰንደቅ የሚተከለው በተቻለ መጠን ከሚተከልበት ተቋም ሕንፃ ፊት ለፊትና መሀል ለመሀል ይሆናል፡፡

## 14. ሰንደቅ ዓላማው ስለሚሰቀልበትና ስለሚወርድበት ጊዜ

1. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/እና/3/ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10/1/ በተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ሰንደቅ ዓላማው ከጠዋቱ በ12 ሰዓት ተሰቅሎ ከምሽቱ 12 ሰዓት ይወርዳል፡፡ ሆኖም የድንጋጌ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በተደነገገባቸው አካባቢዎች ተፈፃሚ ላይሆን ይችላል ፡፡

## 11 . Display of the Flag with other Emblems

1. When carried or hoisted with one or several other Emblems the Flag shall be on the right.
2. When carried or hoisted with only two Emblems, the Flag shall be at the center as higher as its proportional height.

## 12. Tip of the Flag Staff

The Tip of any Flagstaff shall be Semi-Circular in shape.

## 13. Place for Setting up the Flagstaff

The Flagstaff of the Flag flown at a square shall, as far as possible, be set up at the center in front of the institution buildings.

## 14. Time of Hoisting and Lowering the Flag

1. Without prejudice to sub-article (2) and (3) of this Article, the Flag shall be hoisted at 6 a.m. and lowered at 6 p.m. at Offices specified in Article 10(1) of this proclamation. However, in surrounding where a state of emergency has been declared shall not be applicable.

2. በትምህርት ቤቶች ሰንደቅ ዓላማው የሚሰቀለው ጠዋት ተማሪዎች ተሰልፈው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ይሆናል ፤የሚወርደውም ከምሽቱ 12 ሰዓት ይሆናል፡፡

3. በበዓላት ወቅት ሰንደቅ ዓላማው ከዋዜማው እስከ በዓሉ ማግስት የሚሰቀል ሲሆን በነዚህ ቀናትም ጠዋት 12 ሰዓት እየወጣ ከምሽቱ 12 ሰዓት ይወርዳል፡፡

## 15. ሰንደቅ ዓላማው ሲሰቀልና ሲወርድ ሊሠጠው ስለሚገባ አክብሮት

1. በክልሉ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ለብሔራዊ ክልሉ ሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ሰንደቅ ዓላማው ካረጀ ፣ከተቀደደ ወይም በማንኛውም መልኩ ማገልገል ካልቻለ በተገቢው የክብር አፈፃፀም ስርዓት ተቃጥሎ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

## 16. ሰንደቅ ዓላማው ከፌደራሉና ከሌሎች አቻ ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል ስለሚኖረው ሥነ-ሥርዓት

ሰንደቅ ዓላማው ከፌደራሉ እና ከሌሎች አቻ ክልሎች ሰደንቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል ስለሚኖረው የአወጣጥ ስነ-ስርዓት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 ዓ.ም አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2. In schools, the flag shall be hoisted in the morning before classes begin and lowered at 6 p.m.

3. The Flag shall be hoisted on the eve and lowered on the morrow of public holidays, however on each of these days the Flag shall be hoisted at 6 a.m. and lowered at 6 p.m.

## 15. Respect due on Hoisting and Lowering of the Flag

1. Any person reside in the Region shall have the responsibility and duty to pay due honor to the Flag of the National Region.

2. Without prejudice to sub-article (1) of this Article, when the Flag becomes old, worn out or in any way can no longer be used, it shall be destroyed by burning with due respect.

## 16. Procedural Orders of Display of the Flag with the Flags of Federal and Other Regional States

Appropriate provisions of the Federal Democratic Republic of Ethiopia “Flag Proclamation No. 654/2009”shall apply to the procedural orders of the flag with the flags of federal and other Regional States.

## 17. በሰልፍ ጊዜ የሰንደቅ አላማው አያያዝ

ሰንደቅ አላማው በህዝባዊ ሰልፍ ላይ እንዲያዝ ሲደረግ የአያያዙ ስርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ሰንደቅ ዓላማውን የያዘው ሰው ከሰልፈኛው ፊት መሀል ለመሀል አምስት ሜትር ቀድሞ ይሄዳል፡፡
2. ተሸካሚው ሰንደቁን ከታች በቀኝ እጁ ከላይ በግራ እጁ በሰውነቱ መሀል ለመሀል ቀጥ አድርጎ ይይዘዋል፡፡
3. ሰንደቅ ዓላማው ይታጀባል፡፡

## 18. በተሽከርካሪዎች ላይ ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀም

1. የብሔራዊ ክልሉ ፕሬዘዳንት እና የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በሚጓጓዙበት ተሽከርካሪ ላይ ሰንደቅ ዓላማው ይሰቀላል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የብሔራዊ ክልሉን ሰንደቅ ዓላማ በተሽከርካሪ ላይ በመስቀል መጠቀም የሚችሉት የሚከተሉት የስራ ኃላፊዎች ብቻ ይሆናሉ፡-

   ሀ/ የክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ፤

   ለ/ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፤

   ሐ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ፤

   መ/የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት፤

## 17. Procedure at procession

At public procession the procedure of displaying the Flag shall be as follow:

1. The guard of honor in charge of holding the Flag shall come at front with 5 meter distance from the first group raw.
2. The guard of honor shall hold the staff with his right hand at its bottom and his left hand at the upper part by erecting at the center of his body.
3. The Flag shall be accompanied.

## 18. Procedure to Mount and Fly the Flag on Vehicles

1. The Flag shall be flown on the vehicle, in which the President and the Speaker of National Region is traveling.
2. Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the privilege of flying the National Regional Flag on a vehicle is restricted to:

   a. The Deputy Speaker of the Regional Council;

   b. The Vice-head of Government of the Region;

   c. The Members of the council of the Regional Government;

   d. The President and Vice-President of the Regional Supreme Court;

ሠ/ የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር ፤

ረ/ የዞን ዋና አስተዳዳሪዎች እና ፤

ሰ/ የብሔረሰብ ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎች ፡፡

e. The General and Deputy General Auditor of the Region;

f. The Zonal Head of Administrators; and

g. The Speakers of Nationality Council.

## 19. በክልላዊ ሀዘን ቀን ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ ሥነ ሥርዓት

1. በኃላፊነት ላይ ያለ ወይም ከኃላፊነት የተነሣ የክልሉ ፕሬዘደንት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ የብሔራዊ ክልሉ ሰንደቅ ዓላማ በሚታወጀው ክልላዊ የሐዘን ቀን ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ከተመለከተው ውጪ ክልላዊ የሀዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸው ሁኔታዎችን በተመለከተ የክልሉ ምክር ቤት ሊወስን ይችላል ፡፡

3. ክልላዊ የሀዘን ቀኑ በህዝባዊና ሐይማኖታዊ በዓላት ላይ የሚውል ከሆነ ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ አይደረግም ፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ድንጋጌ መሠረት በሚፈፀም የቀብር ሥነ -ሥርዓት ቀብሩ ከመፈፀሙ በፊት በአስከሬኑ ሣጥን ላይ ያረፈው ሰንደቅ ዓላማ በተገቢው ስነ-ስርዓት ተጣጥፎ መነሳት ያለበት ሲሆን በማንኛውም መልኩ መሬት መንካት የለበትም፡፡

## 19. Half–Masting and Regional Mourning

1. In the event of the death of Regional President, on official duty or retirement, the National Region Flag shall be flown at half mast on the declared day of Regional Mourning.

2. Up on the death of persons and dignitaries other than those mentioned under sub-article (1) of this Article, half masting and a Regional mourning day may be held if the Regional Council pass a decision to that effect.

3. In cases where a Regional mourning day coincides with official holiday, the Flag shall not be flown at half mast.

4. On occasions of funeral in accordance with the provisions of this Article, the Flag shall first be folded following the appropriate procedure before the bier or coffin is lowered in to the grave. The Flag may not touch the ground.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ስለተከለከሉና ስለሚያስቀጡ ተግባራት

1. የክልሉን ሰንደቅ ዓላማ ወይም ዓርማ በአደባባይ መቅደድ ፣ ማቃጠል ፣ ማጥፋት መድፈር ፣ ማበላሸት ፣ መስደብ ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ማዋረድ በዚህ አዋጅ የተከለከለ ተግባር ነው ፡፡
2. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል ፡፡

### 21. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

### 22. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

ይህን አዋጅ የሚቃረን አዋጅ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

### 23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም**
**አያሌው ጎበዜ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት**

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 20. Prohibitions and Penalties

1. To worn out at the square, to burn, to hide, to disrespect, to insult or degrades by any other means of the Flag or Emblem of the Region is a prohibited act under this proclamation.
2. Anyone who commits an act in contravention to sub-article (1) of this Article, shall be penalized with the appropriate provisions of penal law.

### 21. Power to Issue Regulations

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

### 22. Inapplicable laws

Any proclamation or customary practice inconsistent with this proclamation, shall be inapplicable on matters provided for in this proclamation.

### 23. Effective date

This proclamation shall come in to force as of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar,**
**This 1st day of April 1, 2011.**
**Ayalew Gobezie**

**President of the Amhara National Regional State**